



# የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ (ኤንኤኤም)







የብዙዮሽና የአለማቀፍ ትብብር ደጋፊ የሆነችው የአዘርባጃን ሪፐብሊክ 28ኛውን የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ የርዕሳነ ብሔሮችና የመሪዎች ጉባኤ ከኖቬምበር 25-26 በባኩ አስተናግዳለች፡፡ ስፋቱን፣ የድርጅቱን የፖለቲካና የኢኮኖሚ አቅምና በአለም ፖለቲካ ላይ ተጽእኖ የማሳረፍ ችሎታውን ግምት ውስጥ በማስገባት የዚህን ሁነት ጉልህ ፋይዳ በቀላሉ ለመረዳት አያዳግትም፡፡ ሪፐብሊኳ በ1991 ነጻነቷን ካስመለሰችበት ከ1991 ወዲህ በአዘርበጃን ታሪክ ምናልባት ትልቁ ካልሆነ ከትላልቆቹ አለማቀፍ የፖለቲካ ሁነቶች አንዱ ነበር፡፡

**የፍላጎት አንድነት**

የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ 120 አገሮችን አንድ የሚያደርግ ነው፡፡ የእነዚህ አገሮች የውጭ ፖለቲካ ሂደት መነሻው በወታደራዊና ፖለቲካዊ ቡድኖች ለመሳተፍ ፈቃደኛ አለመሆንና የነጻነትንና የእኩልነትን መርሆዎች መነሻ በማድረግ የሕዝቦችን በሰላምና በጋራ አብሮ መኖር ለማረጋገጥ በጋራ መሥራት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ድርጅቱ የተመሠረተው በ1955 የእስያና አፍሪካ የባንዱንግ ጉባኤ ሲሆን አዲስ የተመሠረቱ አገሮች ከድሕረ ቅኝ ግዛት ጥገኝነት ነጻ የሆነ ለዘመናዊ ኢኮኖሚ ግንባታ እድል በሚፈጥርና ፍትሃዊና የተሻለ የአለማቀፍ ግንኙነት ሲስተም ለመፍጠር በሚያስችል ሁኔታ የራሳቸውን የልማት አቅጣጫ በሚፈልጉበት ጊዜ ነው፡፡

ከገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ (ኤንኤኤም) መሥራቾች አንዱ የኢንዶኔዥያ ፕሬዚዳንት አሕመድ ሱካርኖ (ከ1945-1967) በአንድ ወቅት ሲናገሩ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ ምሥረታ መነሻው የመልክአ ምድር፣ የዘር ወይም የኃይማኖት አንድነት ሳይሆን "የፍላጎት አንድነት" መሆኑን በአጽንኦት ገልጸዋል፡፡ ጦርነት የሌለባት አለም ፍላጎት- ከሁሉም በላይ፣ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ የተመሠረተው በሁለቱ ጎራዎች መካከል የጂኦፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ርዕዮተ አለማዊ ፍጥጫና በመኃል ሶቪየት ሕብረት (ዩኤስኤስአር) በሌላ በኩል ደግሞ ናይትድ ስቴትስ አሜሪካ (ዩኤስኤ) በመሪነት በተሰለፉበት በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜ ነበር፡፡ ግቡ ለኢኮኖሚና ለማህበራዊ እድገት፣ ለፍትሃዊና ለተመጣጣኝ የልማት ሁኔታ አስተዋጽኦ ማድረግ ነበር፡፡

በባንዱንግ ጉባኤ የወጣው የሉላዊ ሰላምና ትብብር ማስፋፊያ መግለጫ በአገሮች መካከል በሰላም አብሮ መኖርና ትብብር የሚመራባቸውን 10 መርሆዎች አስቀምጧል፡- እነዚህም መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችን እንዲሁም የተ.መ.ድን ቻርተር ግቦችና መርሆዎች ማክበር፤ የሁሉንም አገሮች ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት ማክበር፤ ለሁሉም ዘር እኩልነትና ለሁሉም አገሮች ለትላልቆቹም ለትናንሾቹም እኩልነት እውቅና መስጠት፤ በሌላ አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት መቆጠብ፤ በተ.መ.ድ ቻርተር መሠረት የእያንዳንዱን አገር በግልና በሕብረት ራስን የመከላከል መብት ማክበር፤ በማንኛቸውም ኃያላን መንግሥታት መካከል የሚደረግ ማንኛውንም የጋራ መከላከያ ስምምነት ከመጠቀም መታቀብ፤ በማንኛውም አገር በሌሎች አገሮች ላይ ተጽእኖ ከማሳደር መታቀብ፤ የግዛት አንድነት ወይም የፖለቲካ ነጻነት ላይ የወረራ ድርጊት ወይም የማስፈራራት ድርጊት ከመፈጸም ወይም ኃይል ከመጠቀም መቆጠብ፤ ማንኛውንም አለማቀፍ አለመግባባት በሰላማዊ መንገድ መፍታት፤ የጋራ ጥቅምንና ትብብርን ማስፋፋት፤ ፍትህንና አለማቀፍ ግዴታዎችን ማክበር ናቸው፡፡

**የአለም ሁለት ሶስተኛ**

ዛሬ ከአለም ሕዝብ ወደ 55 በመቶ የሚጠጋው በገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ አባል አገሮች ይኖራል፡፡ እነዚህ አገሮች ከአለም የነዳጅ ኃብት ከ75 በመቶ በላይ፤ ከአለም የጋዝ ኃብት ከ50 በመቶ በላይ፣ ግዙፍ የሰው ኃብትና የተፈጥሮ ኃብት ያላቸው ናቸው፡፡ ማንም ሰው ይህ አቅም በአስተዋይነትና በብልሃት ጥቅም ላይ ከዋለ በአለም ልማት ላይ ተጽእኖ ወደሚፈጥር ኃይለኛ የፖለቲካ ኃይል ሊለወጥ እንደሚችል አጠያያቂ አይሆንም፡፡

አዘርባጃን በንጽጽር በቅርቡ - በ2011 የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ ሙሉ አባል ለመሆን በቅታለች፡፡ አዘርባጃን ገና አባል በሆነች በስምንት አመታት ውስጥ ከአለም ከግማሽ በላይ የሚወክለውን የዚህን ድርጅት ዋና አለማቀፍ ሁነት ማስተናገዷ ያለምንም ጥርጥር እያደገ ለመጣው የአዘርባጃን አለማቀፋዊ ሥልጣን እውቅና መስጠት መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡







፡ አዘርባጃን ከአለም ከግማሽ በላይ የሚወክለውን የዚህን ድርጅት ይህን ዋና አለማቀፍ ሁነት ካስተናገደች ገና ከስምንት አመት በኋላ ያለምንም ጥርጥር እያደገ ለመጣው የአዘርባጃን አለማቀፋዊ ሥልጣን እውቅና መስጠት መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡

በመርህ ደረጃ የቅርብ አመታት ሂደቶችን ብንመለከት ባኩ ከአንድ መቶ በላይ አገሮች ርዕሳነ ብሄሮችና መሪዎች የሚሳተፉበት የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ የስብሰባ ቦታ ሆና መመረጧ በፕሬዚዳንት ኢልሃም አሊዬቭ አመራር የተከናወነውን በአዘርባጃኒ ሕዝብ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ሚዛናዊና ብዝሃነት ያለው የውጭ ፖሊሲ ያስገኘው ውጤትና በሁሉም አካባቢዎች ሪፐብሊኳ ያስመዘገበችው አስደናቂ የስኬት ታሪክ ምክንያታዊ ማሳያ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

**የአዘርባጃን ቀዳሚ ትኩረት**

አዘርበጃን በገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ ተሳታፊ በመሆኗ የአገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ስላስገኘው ውጤት ስንነጋገር በፕሬዚዳንት ኢልሃም አሊዬቭ ትዕዛዝ በግልጽ እንደተገለጸው ይህ ከፌብሩዋሪ 11 ቀን 2019 ጀምሮ እስከመጪው ጉባኤ በአለማቀፍ ሰላም፣ ጸጥታና ትብብር ሂደትና በርካታ የላቲን አሜሪካ አገሮችን፣ የእስያና የአፍሪካ አገሮችን ጨምሮ ከተለያዩ አገሮች ጋር በሚደረግ የሁለትዮሽና የብዙዮሽ ግንኙነት አገራችን የበለጠ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ የምትችልበትን ዕድል ፈጥሯል፡፡

አዘርባጃን ከዘመነኛው ጊዜያት ተጨባጭ እውነታ የሚጣጣም አጠቃላይ ተቋማዊና የአሠራር መሣሪያዎች ማሻሻያና የማላመጃ እንቅስቃሴ ጠንካራ ደጋፊ ነች፡፡ አዘርባጃን ከማንኛውም ውዝግብ ራሷን የምታርቅ፣ የሁለትዮሽና የብዙዮሽ ትብብርን ምሣሌነት ለመምራት የምትሞክር አገር ነች፡፡ ዛሬ አዘርበጃን ሙሉ በሙሉ የተለያየ አጀንዳ ያላቸው አገሮች የጋራ መግባቢያ ለማግኘት የሚሞክሩ ወገኖች በሚሳተፉበት ሉላዊ የጸጥታ መድረክ የራሷን ሚና ትጫወታለች፡፡

አዘርባጃን የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ አባል ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ ይህ ድርጅት በአለማቀፍ ደረጃ እውቅና ላገኘው የአዘርባጃን ሉአላዊነት፣ የግዛት አንድነትና የማይደፈር ድንበር ድጋፉን በማያሻማ ሁኔታ ገልጾአል፡፡ የድርጅቱ ሁሉም ሰነዶች አገራችን የምትሰቃይበት ዋነኛ ችግር- የአርሜኒያ-አዘርባጃኒ የናጎርኖ ካራባክ ግጭት- እነዚህን መርሆዎች በመከተል በሰላማዊ መንገድ መፈታት እንዳለበት ጥሪ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ ይህ በጁላይ 2019 በካራካስ፣ ቬንዙዌላ በተካሄደው የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ የመጨረሻ ሰነድም በግልጽ ተረጋግጧል፡፡ ሰነዱ የአዘርባጃንን አቋም የሚደግፍ የተለየ አንቀጽ ይዟል፤ በተመድ የጸጥታው ምክር ቤት አግባብ ያላቸው ውሣኔዎች የተላለፉ ቢሆንም በአርሜኒያና በአዘርባጃን መካከል ያለው ግጭት እስካሁን ገና ባለመፈታቱ በአለማቀፍና በክልሉ ጸጥታና ሰላም ላይ ስጋት ደቅኗል ሲል ይገልጻል፡፡ አሁንም በድጋሚ በተመድ ቻርተር የተገለጸውን ኃይል ያለመጠቀም ፖሊሲ አስፈላጊነት በማረጋገጥ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ የሚኒስትሮች ስብሰባ ግጭቱን በግዛት አንድነት፣ ሉአላዊነትና አለማቀፍ ደረጃ እውቅና ባገኘ የአዘርባጃን ድንበር ማዕቀፍ በድርድር መፍታት የሚቻልበት መንገድ መፈለግ እንዳለበት ጥሪ አቅርቧል፡፡ ይህ ከፕላኔቷ ከሞላ ጎደል ሁለት ሶስተኛውን የሚሸፍኑት የአለም 120 አገሮች አቋም ነው!

የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ ጉባኤው ለአዘርባጃን ረጅም ጊዜ የቆየው ግጭት፣ አሁን ባለው አለም ባልተለመደ (“ደብል ስታንዳርድ”) ሁኔታ ከአዘርባጃን ግዛት 20% በወረራ ይዛ የቀጠለችው አርሜኒያ በያዘችው አፍራሽ አቋም የተደናቀፈውን መፍትሄ፣ በወራሪ ላይ ተእጽኖ ለማሳረፍ የሚረዳ የሕግና የአሠራር ሥርአት ችግር ያለበት ወይም የሌለ ስለመሆኑ፣ በሰለጠነ ልማድ ማዕቀፍ ተፈጻሚ የማድረግን አስፈላጊነት በሚመለከት የአለምን ህብረተሰብ ትኩረት ለመሳብ ሌላ አመቺ እድል ፈጥሯል፡፡

አዘርበጃን ቀደም ሲል የድርጅቱ በሊቀመንበር በምትመራበት ጊዜ ቅድሚያ ትኩረት የምትሰጣቸውን ነጥቦች በዝርዝር አስቀምጣለች፤ እነዚህም፡- በአለማቀፍ ግንኙነት ሥርአት የንቅናቄውን ሚናና ሥልጣን ይበልጥ ማሳደግ፣ በአለማቀፍ ደረጃ የሚመራባቸውን መሠረታዊ መርሆዎች











ማስፋፋት፣ በህግ የበላይነት፣ አለማቀፍ ሕጎችንና የባንዱንግ መሠረታዊ መርሆዎች በማክበር ላይ የተመሠረተ የበይነ መንግሥታት ግንኙነት ምሥረታን ማስፋፋት፣ ለፕላኔታችን ሰላም፣ ጸጥታና ዘላቂ ልማት ለማጠናከር አስተዋጽኦ ማድረግ የሚሉ ናቸው፡፡

**ለተሻለ አስተማማኝና ፍትሃዊ አለም**

በአለም የሚካሄዱ ሂደቶች አኪያሄድ አመክንዮው አለም በብዙ መስኮች እየተከፋፈለች በመጣችበት፣ ተቃዋሚ ቡድኖችና ቅንጅቶች በአለም የጂኦፖለቲካ ካርታ እንደገና ብቅ ማለት በጀመሩበት ባሁኑ ጊዜ ከቀዝቃዛው ጦርነት ፍጻሜ በኋላ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ ሚና እየቀነሰ መጥቷል፣ ወደፊትም የበለጠ የመቀነስ አዝማሚያ እንደሚያሳይ ይገመታል፡፡ አሁን ያለው የአለም ሥርአት እንደገና በመውደቅ ላይ ይገኛል፤ አዳዲስ የኃይል ማዕከሎች እየመጡ ነው፣ በመንግሥታት መካከል ያሉ ግንኙነቶች በአዲስ መልክ እየተቀረጹ ነው፤ የረጅም ጊዜ ቅራኔዎች ሥር እየሰደዱ ነው፣ የረጅም ጊዜ ተፎካካሪዎች የሚጣጣሙ ጂኦፖለቲካዊና ኢኮኖሚዊ ጥቅሞችን መነሻ በማድረግ በጋራ የሚግባቡበትን ቋንቋ እያገኙ ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ በአዲሱ የአለም ሥርአት መዋቅር ሚዛናዊና አቃቢ ኃይል መሆን የሚችልበትን ቁመናና አቋም ይዞ መገኘት የሚችልበትን መንገድ መፈለግ አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ ድርጅት የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ ቅይጥ ባህርይ ያለው ነው፣ ይህም ሙሉ በሙሉ በተለያየ የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ አገሮችን፣ የመንግሥት ተቋማትን የብስለት ደረጃ፣ የውስጥ መረጋጋትንና የሕዝቡን ማህበራዊ ደህንነት፣ በተወሰኑ አለማቀፍ ችግሮች ላይ ያላቸውን የአመለካከት ልዩነት ይጨምራል፡፡ ሆኖም በገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ (ኤንኤኤም) የሚሳተፉ ሁሉም አገሮች የልማት ሞዴሎች ከውጭ በማይጫኑበት፣ አገሮች በተወሰኑ ሁኔታዎች እንዴት ያለ ባህርይ ማሳየት እንዳለባቸው፣ ከሌሎች አገሮች ጋር እንዴት የውጭ ግንኙነት መፍጠር እንዳለባቸው፣ ከማን ጋር ወዳጅነትና አጋርነት መፍጠር እንዳለባቸው፣ የተፈጥሮ ኃብታቸውን እንዴት ጥቅም ላይ ማዋል እንዳለባቸው ነጋሪ አዛዥ በማያስፈልጋቸው በተሻለና የበለጠ አስተማማኝ በሆነ አለም መኖር ይፈልጋሉ፡፡ በጦርነት ምክንያት የሚመጣ ጥፋትና የእልቂት ስጋት በላያቸው ላይ በማያንዣብብበት፣ የውጭ ጣልቃ ገብነት ወደግጭት፣ የእርስ በርስ ጦርነትና ወደሚሊዮኖች ስደተኞች መፈናቀል በማያመራበት አለም መኖር ይፈልጋሉ፡፡ በጋራ በመተባበር የፖለቲካ ቁርጠኝታቸውን በተግባር ማሳየት፣ ፕላኔታችንን ወደ ማያቋርጥ የጦር መሣሪያ እሽቅድድም፣ ከባድ ፍጥጫና ማዕቀብ የመለወጥ ፍላጎት ያላቸውን ኃይሎች መቃወም




የእነዚህ አገሮች ጉዳይ ነው፡፡

“የአለም ሰላምን መረጋጋትንና ዘላቂ ልማት ማስፋፋት” በሚል ርዕስ ባለፈው ኤፕሪል በባኩ በተካሄደው የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ የሚኒስትሮች ስብሰባ የአዘርባጃን ፕሬዚዳንት ኢልሃም አሊዬቭ ባደረጉት ንግግር በአጽንኦት እንደገለጹት “እርስ በርሳችን መደጋገፍ አለብን፡፡ ተመሳሳይ ተግዳሮቶችና ችግሮች ተደቅነውብናል ማለት ይቻላል፡፡ በተወሰነ ሁኔታ ያለፍንበት ታሪክም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁላችንም የየራሳችንን ነጻ ሕይወት መኖር ነው የምንፈልገው፡፡ ከመካከላችን ማንኛውንም አይነት ሥራ እንድንሠራ ማንም እንዲጠይቀን የሚፈልግ፣ በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ ለመግባት፣ ማድረግ ያለብን እንዲነገረን የሚፈልግ ማንም የለም፡፡ በጋራ ከተባበርን ብቻ ነው ጠንካራ መሆን የምንችለው”፡፡

ለዚሁ ጉዳይ የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ እንቅስቃሴዎቹን ማጠናከር ያስፈልገዋል፡፡ በአጋጣሚ ይህ ጊዜ አዘርባጃን የገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ (ኤንኤኤም) የወቅቱ ሊቀመንበር ከሆነችበት ጊዜ ጋር ተገጣጥሟል፡፡ ከዚህ አንጻር የአዘርባጃን የወቅቱ ሊቀመንበርነት በገለልተኛ አገሮች ንቅናቄ ውሣኝ ታሪካዊ ዕድል የሚፈጥር ነው፡፡

(የተርጓሚው ማስታወሻ፡- በዚህ መጣጥፍ የተጠቀሰ ዘመን ሁሉም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው፡፡)